# የእግዚአብሔር ህላዌ

ከቀሲስ/መኩብብ አትናው

የፍጥረት ሁሉ አስገኝ የሆነ ፣ ሁሉን ማድረግ የሚችል አንድ አምላክ መኖሩ በድንቅ ሥራዎቹ የተገለጠ ሐቅ መሆኑ ከዘመናችን በፊትም ሆነ በአሰንበት ዘመን በማያዳግም ሁኔታ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታመነ ስለሆነ አያከራክርም ። ዋናው አከራካሪ ጉዳይ ሰዎች እንዴት እርሱን ማወቅ እንደሚችሉ ከማሳመን ላይ ነው ። ይኸውም ሰው በመንፈስ እስከሚተሰምስበት ጊዜ ድረስ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል በእምነት ከመቀበል ይልቅ በዓይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ ግዙፍ ማስረጃ ይፈልጋል ። ባጠቃላይ አንዳንዶች እግዚአብሔርን በአካል በዓይን አይቶ ማንነቱን ለይቶ ለማወቅ ይፈልጋል ።

ነገርግን "እግዚአብሔር መንፈስ ነው፡- የሚሰግዱለትም ሁሉ በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ይገባል" (ዮሐ. 4.24) ተብሎ ተጽፎአልና እርሱን በአካል ሳይሆን በመንፈስ ማየት ብፁዕነት ነው ። ኢየሱስ ቶማስን "ስለአየኸኝ አመንህ? ነገር ግን ሳያዩኝ የሚያምኑ ብፁዓን ናቸው" ሲል የሰጠው የማያዳግም ትምህርት ለመላው የሰው ዘር መመሪያ ሆኖ የሚያገለግል ነውና (ዮሐ.20 28-29) አስቀድሞም በዘመነ ብሉይ ሙሴ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት በአካል ማየት ፈልጎ በጸሎት ጠይቆ ነበር ። ታዲያ ከእግዚአብሔር የተሰጠው የቃል በቃል መልስ " ሰው አይቶኝ በሕይወት መኖር አይችልምና ፊቴን ማየት አይቻልህም ... ጀርባዬን ግን ታያለህ" ብሎት እንደነበረ በኦሪት ዘፀአት 33.20-23 ተጽፎአል ። ወንጌላዊው ዮሐንስም እግዚአብሔርን ምን ጊዜም ቢሆን ከቶ ያየው የለም" ሲል የጻፈውም ስለዚህ ነበር ፡ (ዮሐ.1፡18)

ዛሬ ግን እግዚአብሔር ለሙሴ ሲነግረው "ፊቴን ማየት አትችልም ፡ ጀርባዬን ግን ታያለህ ያለውን ቃል ስንመረምር እግዚአብሔር በአካል መታየቱን የሚጠቁም ምልክት እናያለን ። በፈረንጆችም አነጋገር እንዲ "ጀርባህን አይተኸዋል ወይ?" የሚል ምሳሌያዊ የቅኔ ንግግር ፈሊጥ አለ ። ትርጉሙም "ልጅ ወልደሃል ወይ?" ማለት ነው ። ምክንያቱም ሰው በስተኋላው ያለውን አካል ወይም ጀርባውን ማየት የሚችለው ከርሱ የተወለዱት ልጆች የሚወለዱትን እምሳያ በመመልከት ሊሆን ይችላልና ነው በዚህም አመለካከት ስንመራ እንደ እግዚአብሔር አምላክ ጀርባ አድርገን የምናስበው አንድ ልጁ ክርስቶስ መሆኑ ነው እርሱ በሥጋ ተገልጧልና ስለዚህም ራሱ ክርስቶስ ሲናገር እኔን ያየ አብን አየ " ብሏልና በክርስቶስ አማካይነት የእግዚአብሔርን ጀርባ ብቻ ሳይሆን ፊቱንም ለማየት የበቁ ሰዎች እንደነበሩ እንጠራጠርም ፡ የነርሱም ዓይን የእኛ ዓይን ስለሆነ በሰውን ምስክርነት ስናምን ነፍሳችን ከእግዚአብሔር ጋር በመንፈስ ገጽ በገጽ መተያየት ትጀምራለች ማለት ነው ።

ከዚህም በቀር እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ በሰው አምሳል ይገለጥ እንደነበርና አሁንም ከኃጢአት መጋረጃ ውጭ የሆኑ በመንፈስ ልባቸውን ላነፁ ቅዱሳን ሁሉ በሰው አምሳል ተገልጦ የሚያነጋግራቸው ስለመሆኑ በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ የጽሑፍ ማስረጃዎች አሉ ። ይህንም ነቢዩ ኢሳይያስ ሲያስረዳ በደላችሁ (ኃጢአታችሁ) በእናንተና በአምላካችሁ መካከል የልዩነት መጋረጃ ሆናለች ጸሎታችሁንም እንዳይሰማ ኃጢአታችሁ ፊቱን ከናንተ ወደሌላ ተመልሰዋለች (ሰውሮታል) ምክንያቱም ሁለ ንተናችሁ በኃጢአት ረክሶአል ፡ ከንፈ ንተናችሁ በኃጢአት ረክሶአል ፡ ከንፈራችሁም ሐሰትን ተናግሮአል ። ምላሳችሁ ሐሰትን ሸርቦአል ፦ በጽድቅ የሚጸልይ ፡ በእውነትም የሚፈርድ የለም ጉዳትን ወንሰዋል ፡ በደልንም ወልደዋል ...በማለት ይወቅሳል ። ከዚህም አባባል የምንረዳው ዋና ነገር ሰውንና እግዚአብሔርን የበረት መጋረጃ ሆኖ የለያያቸው ከመጀመሪያው ሰው ወድቀት በኋላ ወደ ዓለም ገብቶ ለብዙ ዘመናት ይልቅ የቆየው የኃጢአት ክምር መሆኑን ነው ። ኃጢአት ባይኖር ሰው እግዚአብሔርን ፊት ለፊት ማየት ይችል ነበር ማለት ነው ። ሰው በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር ጋር ነበርና ነው ። ታዲያ በገዛ ኃጢአቱ የተሠወረበትን ኃይል እንደገና ለማግኘት በቅድሚያ የራሱን የተፈጥሮ ደካማነትና ውስንነት በመመርመርና ጉድለቱን በመገንዘብ ፈንታ በዓይኔ ካላየሁት ፡ በእጄ ካልዳሰስሁት መኖሩን አላምንም ማለት ትክክለኛ አመለካከት አይደለም ።

የአንድን ኃይል መኖርና አለመኖር የሚወስነው በዓይን የማየትና ያለማየት ጉዳይ አይደለምና ነው ። ነፋ ዓይን ያላያቸው የሰውም እጅ ያልዳሰሳቸው በየጊዜው በመከሠት ላይ ያሉ አዳዲስ ነገሮች መኖራቸውን ግዴታ ራሱ ያረጋግጥ የለም እንዴ ? እንግዲያስ እግዚአብሔርን በዓይን ሥጋ ካላየነው አናምንም ማለት አይገባንም ። እርሱን እንዳናየው የጋረደን የራሳችን በደል እንጂ ሌላ ኃይል አይደለምና ።

ለአባባችን ማጠቃለያ በማቴ. 5.8 "ልበ ንጹሖች ብፁዓን ናቸው ፡ እግዚአብሔርን ያዩታልና ተብሎ የተጻፈውን ሕያው ቃል በማስታወስ በፍጥረቱና በንቢያት ፡ ኋላም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት ራሱን የገለጠ ኃያል አምላካችንን በመንፈስ እንድናገለግለው ቅዱስ ፈቃዱ መሆኑን የምንገነዘብበት ከብረት የጠነከረ እምነት ሊኖረን ይገባል ።